# የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

**የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 856/2014**

በኢትዮጵያ ፍትሕ ሚኒስቴር

## የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመርያ ቁጥር 856/2014

የስፖርት ውርርድ ሎተሪን ጥብቅ በሆነ ሕግና ስርዓት እንዲመራ ማድረግና ቁጥጥሩን ማጠናከር በማስፈለጉ፣

ቀደም ሲል በነበረው መመሪያ ያልተካተቱ ተጨማሪ ክልከላዎች ማካተት በማስፈለጉ፣

የአዲስ ፈቃድ ማውጫ፣ የፈቃድ እድሳት ክፍያና የማህበራዊ አገልግሎት ክፍያ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአለም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ህጎች ከደረሰቡት የእድገት ደረጃ ጋር ተቀራራቢ ለማድረግና በአወራራጁና በተወራራጁ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 21 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 83/2005ን በዚህ መመሪያ አሻሽሏል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

*አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመርያ ቁጥር **856/2014** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

*አንቀጽ 2.ትርጓሜ*

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡-

1/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ናቸው፡፡

2/ "አስተዳደር" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው፡፡

3/ "የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡

4/ "የስፖርት ውርርድ ሎተሪ" ማለት በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጪ በተዘጋጁ ሁነቶች የስፖርት ውድድሮችን መሠረት በማድረግ የሚካሄድ ውርርድና ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥ የሎተሪ አይነት ነው፡፡

5/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው

አካል ነው፡፡

6/ "ፈቃድ" ማለት የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለማካሄድ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሠጥና በየዓመቱ የሚታደስ ፈቃድ ነው፡፡

7/ "ደንብ" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 ነው፡፡

8/ "ውል" ማለት በፈቃድ ሰጪው በአስተዳደሩና በፈቃድ ተቀባዩ ወይም ፈቃድ ጠያቂዎች መካከል በተሰጠው የስፖርት ውርርድ ስራ ላይ የሚፈፀም ጋራ የስምምነት ውል ነው፡፡

9/ "የገቢ ግብር አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

10/ "ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 57 መሠረት ከዕድል ጨዋታ የተሰበሰበ ገቢ ተቀባይ ነው፡፡

11/ "የአስተዳደሩ የቁጥጥር ባለሙያዎች" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ያወጡ ግለሰቦችን /ድርጅቶችን/ በስፖርት ውርርድ ሎተሪ መመሪያው መሠረት እያካሄዱ መሆኑን የሚከታተሉና የሚቆጣጠሩ እንዲሁም ህገወጥ የሎተሪ ጨዋታዎችን የሚቆጣጠሩ ባለሞያዎች ናቸው፡፡

12/ "ጠቅላላ ገቢ" ማለት በስፖርት ውርርድ ሎተሪ ከሚሳተፉ ተወራራጆች ከቫት በፊት የሚገኘው ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ማለት ነው፡፡

13/ "የተጣራ ገቢ" ማለት የስፖርት ውርርድ ሎተሪ የሚያካሄደው ሰው ለውርርዱ አሸናፊዎች የሚያወጣውን ወጪ እና ሌሎች ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ቀንሶ ከስፖርት ውርርዱ ሎተሪ ጠቅላላ ሽያጭ የሚያገኘው የተጣራ ገቢ ነው፡፡

14/ "የውጤት መግለጫ" ማለት ፈቃድ ጠያቂዎች በዝርዝር የሚያቀርቡአቸውና የሚጠቀሙባቸው አለም አቀፍ አወራራጆች ውጤት የሚገልጹባቸው ድረገፅ ወይም ዌብሳይቶች ናቸው፡፡

15/ "ተማሪ" ማለት ለዚህ መመርያ አፈጻጸም በሀገሪቱ የአንደኛ፣ መለስተኛና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከታተል ሆኖ የተማሪ የደንብ ልብስ የለበሰ ማለት ነው፡፡

አንቀጽ 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን ውስጥ በስፖርት ውርርድ ሎተሪ ሥራ ዘርፍ በሚሰተፉ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ፈቃድን በተመለከተ

### አንቀጽ 4. ፈቃድ ለመውሰድ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ ማንኛውም ሰው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለማካሄድ ሲፈልግ ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የፈቃድ ጥያቄውን ለዚሁ የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ፈቃድ ጠያቂው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የሥራውን አጠቃላይ መግለጫ ምክረ ሀሳብ፣

ለ) ህጋዊ የቤት ኪራይ ውል ወይም የቤት ባለቤት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣

ሐ) ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችል በባንክ ስቴትመንት የተረጋገጠ መነሻ የስራ ካፒታል ወይም የጥሬ ገንዘብ ማስረጃ፣

መ) ድርጅቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /ፒ.ኤል.ሲ/ ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተመዘገበ የመተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሁፍ፣

ሠ) አመልካቹ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የውርርዱን /የጨዋታውን/ ህግ፣ የውርርድ ውጤት መግለጫ የመረጃ ምንጮችን በምክረ ሀሳቡ ውስጥ ማመላከት አለበት፣

ረ) ሕጋዊ ከሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ለማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ ለማድረግ የተገባ ውል፣

ሰ) በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ብር 1,500,000.00 /አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሺ. ብር /፣

ተ) ሌሎች ፈቃድ ለማግኘት ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡፡ አስተዳደሩም ሌሎች መሟላት አለባቸው የሚላቸውን መረጃዎች በማንኛውም ጊዜ ሊጨምር ይችላል፡፡

ቸ) ድርጅቱ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ በኦንላይን የባንክ የክፍያ አማራጭ የሚያጫውት ከሆነ ከባንክ ጋር ሲዋዋል የማረጋገጫ ደብዳቤውን ለአስተዳደሩ ማቅረብ እንዳለበት መስማማት አለበት፡፡

ቀ) አመልካቹ ያቀረባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ በአስተዳደሩ የሚፈለጉ ሌሎች ግዴታዎችና ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ ተደርጎ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 5. ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ

አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ጥያቄ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀት (2) ስር የተገለጹ ት ዝርዝር መረጃዎችና ማስረጃዎች ተሟልተው ካልቀረቡ ፈቃድ አይሰጠውም፡፡

## አንቀጽ 6. ፈቃድን ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

ማንኛውም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ እንዲያካሂድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡-

1/ ፈቃድ የሚያሳግዱ ሁኔታዎች

ሀ) ባለፈቃዱ በተሰጠው ፈቃድ ከአስተዳደሩ የስፖርት ውርርድ መመሪያ ውጪ ሲሰራ ከተገኘ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚታዩበትን ጉድለቶች በማስመልከት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ፡-

(1) በመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ደርሶት በ7 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እንዲሁም፣

(2) በድጋሚ የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ተደርጎ በሌላ ሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የማስተካከያ ሥራ ካልሰራ የማገድ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ለ) የስፖርት ውርርድ ሎተሪውን አካሄድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለተሰማሩ የአስተዳደሩ የቁጥጥር ባለሙያዎች መረጃ እና ማስረጃ በመስጠት ለመተባበር ፍቃደኛ ካልሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ካላስተካከለ ይታገዳል፡፡

ሐ) በሥራው ላይ ፍርድ ቤት የእገዳ ትዕዛዝ ከሰጠ እግዱ እስከሚነሳ ወይም በጉዳዩ ላይ ዘላቂ ውሳኔ እስከሚሰበጥ ድረስ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፡፡

መ) ማንኛውም ባለፈቃድ ቅርንጫፉ ወይም ዋናው ቢሮ በዚህ መመርያ መሰረት ካልሰራ ይታሸጋል፡፡

2/ ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች

ሀ) ፈቃድ ለመውሰድና ለማደሻ የቀረበ ሰነድ ሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ለ) አስተዳደሩ የሰጠውን ፈቃድ ለሦስተኛ ወገን በማንኛውም መንገድ አሳልፎ ከሰጠ፣

ሐ) በተሰጠው ፈቃድ ላይ ሥራውን ሳይጀምር ለሁለት ወራት /60 ቀናት/ ያህል ጊዜ ከቆየ፣

መ) ለሶስት ተከታታይ ወራት የአስተዳዳሩን ኮሚሽን ሳይከፍል ከቆየ፣

ሠ) ማንኛውም ባለፈቃድ ያለ በቂ ምክንያት ለአንድ ወር ስራ ካቆመ ፤

ረ) የስፖርት ውርርድ ሎተሪ የስራ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በ60 /በስልሳ/ ቀናት ውስጥ ለማቅረብ ካልቻለ፤

ሰ) በተለያዩ ምክንያቶች ታግዶ የቆየው ድርጅት በአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የእርምት እርምጃ ወስዶ ካልተገኘ ወይም

ቀ) ፈቃዱ በበጀት ዓመቱ እስከ ጥር 30 ድረስ ካልታደሰ የሚሰረዝ ይሆናል።

*3/ ፈቃድ ስለሚመለስበት ሁኔታ*

ሀ) ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው ውሳኔው ከፀናበት ቀን ጀምሮ ባሉት በ7 /ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የተሰጠውን ፈቃድ ለአስተዳደሩ የመመለስ ግዴታ አለበት።

ለ) ፈቃድ ስለመታገዱ ወይም ስለመሰረዙ የአስተዳደሩ ደብዳቤ በደረሰው 10 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል። ነገር ግን ቅሬታውን በ10 ቀናት ውስጥ ካላቀረበ ውሳኔው የፀና ይሆናል።

*አንቀጽ 7. ፈቃድ ዕድሳትን በተመለከተ*

1/ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ የሥራ ፈቃዱ በየዓመቱ ከህዳር 1 እስከ ታህሳስ 30 ቀን ባለው ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት።

2/ የስፖርት ውርርድ አወራራጆች ለፈቃድ ዕድሳት ሲመጡ የኮሚሽን ክፍያና የማህበራዊ ድጋፍ ስለማድረጋቸው ማስረጃ፣ የታደሰ የውል ማስከበሪያ የታደሰ የንግድ ፈቃድና የገቢ ግብር ክሪላንስ መቅረብ አለበት።

*አንቀጽ 8. <u>የፈቃድ ማውጫ እና ዕድሳት ክፍያ</u>*

ማንኛውም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ አዲስ ፈቃድ ጠያቂ ሰው ለፈቃድ ማውጫ አገልግሎት የብር 500,000 /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በቅድሚያ መክፈል የሚኖርበት ሲሆን ለነባር ፈቃድ ዓመታዊ የፈቃድ ዕድሳት ደግሞ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ክፍያ ይፈጽማል።

## ክፍል ሦስት

## ጠቅላላ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

*አንቀጽ 9. ልዩ ልዩ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች፡-*

1/ ማናቸውም በስፖርት ውርርድ ሎተሪ ጨዋታ አሸናፊ ሆነው ለቀረቡ ዕድለኞች ክፍያ በህጋዊ ደረሰኝ መፈፀም አለበት፡፡

2/ የጨዋታው አሸናፊ አሸናፊነቱ ታውቆ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ቀናት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሽልማቱን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ ከዕድል ሙከራ ከተገኘ ገቢ 15% ኮሚሽንና ከዕድለኞች የሚቀነስ 15% የገቢ ግብር ክፍያ ለአስተዳደሩ በየወሩ መክፈል አለበት፡፡

4/ አንድ የአሸናፊ ቲኬት ዋጋ የሚኖረው ለ30 ቀናት ብቻ ነው፡፡

5/ ማንኛውም ባለፈቃድ የአሸናፊ ቲኬት ዋጋ የሚኖረው ለ30 ቀናት ብቻ ነው የሚል መልእክት ለደንበኛው በሚሸጠው ትኬት ላይ ወይም በሌላ መንገድ መግለጽ አለበት፡፡

6/ የአስተዳደሩን ኮሚሽን ክፍያ፣ የበጎ አድራጎት ክፍያ፣ የገቢ ግብር ክፍያ እና የአሸናፊ የዋስትና ክፍያ ለማስጠበቅ በቅድመ ሁኔታ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ብር 1,500,000.00 /አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሺ ብር / ማቅረብ አለበት፡፡

7/ ባለፈቃዱ በአንድ የስፖርት ውርርድ ጨዋታ ለአንድ የውርርድ ተጫዋች መክፈል የሚችለው ከፍተኛው የሽልማት ጣርያ ከብር 1,000,000.00 /አንድ ሚሊየን ብር/ መብለጥ የለበትም፡፡

8/ ባለፈቃዱ ቅርንጫፍ ሲከፍት ወይም ሲዘጋ ለአስተዳደሩ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

9/ ድርጅቱ የይለፍ ቁጥር (የሲስተም አክሰስ ኮድ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

10/ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ የሚካሄድበት የስፖርት ጨዋታ በተለያየ ምክንያት ባይካሄድ፣ ቢቋረጥ፣ ቢሰረዝ ደንበኛው የተወራረደበት ጨዋታ አንድ ከሆነ ገንዘቡ መመለስ አለበት፡፡

11/ ተወራራጁ ያስያዛቸው ጨዋታዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ ያልተካሄዱት የተሰረዙ ጨዋታዎች ወጥተው ውጤቱ በተቀሩት ጨዋታዎች ይወሰናል፡፡

12/ አወራራጁ በማንኛውም ጨዋታ ለደንበኛው ትኬት ቆርጦ ከሰጠ በኋላ ደንበኛው ያሸነፈበትን ትኬት ይዞ ሲቀርብ ሌላ የተለየ ችግር ከሌለ በስተቀር ክፍያ ላለመፈፀም የሲስተም ችግር ነው የሚል ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

13/ የሂሳብና ሌሎች ሰነዶች በአስተዳደሩ በተጠየቀ በማናቸውም ጊዜ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

14/ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ በሚካሄድበት ቦታ ማንኛውንም ሌሎች የዕድል ሙከራ ጨዋታዎችን እንዳይካሄድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

*አንቀጽ 10. ስለጨዋታው ተሳታፊዎች*

ማንኛውም ዕድሜው 21 እና ከ21 ዓመት በላይ የሆነ ሰው በጨዋታው መሳተፍ ይችላል። ሆኖም በተጠቀሰው የዕድሜ ክልል በጨዋታው መሳተፍ የሚችሉት በህግ ውል ለመዋዋል ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው።

*አንቀጽ 11. የኮሚሽን ክፍያ*

ባለፈቃዱ ከስፖርት ውርርድ ሎተሪ ትኬት ሽያጭ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 15% ተሰልቶ ለአስተዳደሩ የኮሚሽን ክፍያ መፈጸም ያለበት ሲሆን አፈፃፀሙም ወር በገባ እስከ እስከ አስራ አምስተኛው ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ በአካል በመቅረብ ኮሚሽን መክፈል አለበት።

*አንቀጽ 12. የገቢ ግብር አከፋፈል*

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 57 መሠረት ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ እና ከ1,000.00 ብር በላይ የሆነ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ጨዋታ ለአሸናፊ ከሚሰጥ ሽልማት ላይ 15% የገቢ ግብር በባለፈቃዱ አማካይነት ተሰብስቦ በአስተዳደሩ በኩል ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ መደረግ አለበት።

አንቀጽ 13. በስፖርት ወርርድ ማህበራዊ ዓላማን ስለማስፈፀም

1/ ባለፈቃዱ ከስፖርት ውርርድ ሎተሪ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 0.5% የጋራ ማህበራዊ ዓላማን ለማስፈፀም ያውላል።

2/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ከተገለጸው 0.5% ውስጥ 0.25% ድጋፍ ከሚያደርግለት አካል ጋር ህጋዊ የድጋፍ ውል በመፈጸምና ይህንኑ ማስረጃ ለአስተዳደሩ በማቅረብ ለስፖርት ክለብ /ቡድን፣ ለስፖርት ተቋማት፣ ለጋራ ማህበራዊ ዓላማ ወይም በጎ ተግባር እንዲውል ያደርጋል።

3/ ቀሪውን 0.25% ደግሞ አስተዳደሩ በስፖርት ወይም ተዛማች ስራ ላይ ለተሰማሩ ተቋማት ማዋል እንዲችል ለአስተዳደሩ በየወሩ ገቢ ያደርጋል። አስተዳደሩም ከሚመለከተው ተቋም ጋር በሚፈጽመው ህጋዊ ውል መሰረት ድጋፍ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

## ክፍል አራት

## *ክትትልና ቁጥጥር ስለማድረግ*

*አንቀጽ 14.<u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>*

1/ አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ /የተመለከቱ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል።

2/ የአስተዳደሩ ተቆጣጣሪ ሠራተኞች የተሰጣቸውን የሥልጣን ማረጋገጫና መታወቂያ ወረቀት ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት ድርጅት ባለቤት፣ ወኪል፣ አጫዋች ሠራተኞች በማሳየት በማናቸውም ውርርድ በሚካሄድበት ቦታ ቁጥጥር ያደርጋሉ። ተቆጣጣሪ ሠራተኞቹ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጨዋታውን የይለፍ ቁጥር /የሲስተም አክሰስ ኮድ/ ተጠቅመው በጨዋታው ዌብሳይት ላይ ቁጥጥር ሲያደርጉ ያደርጋሉ።

አንቀጽ 15.<u>ውል ስለመግባት</u>

አመልካቹ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱ ድንጋጌዎችን ሳይሸራረፉ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከጨረሰ በኋላ ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት ከአስተዳደሩ ጋር ውል ይፈፅማል በውሉም መሠረት ይተዳደራል።

## ክፍል አመስት

## *ክልከላ እና ቅጣት*

*አንቀጽ 16.<u>የተከለከሉ ጉዳዮች</u>*

1/ ማንኛውም ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ ሰው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ መወራረድ የተከለከለ ነው።

2/ አስተዳደሩ እውቅና ከሰጠው ቅርንጫፍ ውጭ ማወራረድ የተከለከለ ነው።

3/ የስፖርት ውርርድ ጫት ቤት ግሮሰሪ ባርና ሪስቶራንት መሰል ቦታዎች ማጫወት የተከለከለ ነው።

4/ የስፖርት ውርርድ ዋናው ቢሮና ቅርንጫፍ ከእምነት ተቋማትና ከት/ቤት 500 መቶ ሜትር ክልል ውስጥ የስፖርት ውርርድ ድርጅት መክፈት የተከለከለ ነው።

5/ አስተዳደሩ ካወጣው ለቢሮ የሚያበቃ መመዘኛዎች /ስታንዳርድ/ ውጪ የስፖርት ውርርድ ቅርንጫፍ መክፈት የተከለከለ ነው።

6/ በስፖርት ውርርድ ሎተሪ መጫወቻ ስፍራ በእድሜ ገደብ ሳይወሰን የተማሪ ደንብ ልብስ /ዩኒፎርም/ ለብሶ በውርርድ እንዲሳተፉ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 17.የክፍያ ግዴታን አዘግይቶ በመክፈል የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጫ

ባለፈቃዱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአስተዳደሩ የሚጠበቅበትን ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ያልከፈለ እንደሆነ የሚከተለውን አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲፈፀምበት ይደረጋል፣

1/ ባለፈቃዱ ወር በገባ በተከታታይ በ15 ቀናት ውስጥ በአካል ቀርቦ ከሚፈለገው ሰነድ ጋር የሚፈለግበትን ክፍያ ሳይፈፅም ቀኑ ካለፈ እስከ ቀጣዩ 21 ቀን ውስጥ የክፍያውን 20% መቀጫ ጨምሮ ይከፍላል፡፡

2/ ለሁለት ተከታታይ ወራት የሚፈለግበትን ክፍያ ሳይፈጸም ከቀረ 50% መቀጫን ጨምሮ ይከፍላል፡፡

3/ ባለፈቃዱ የሚፈለግበትን ክፍያ ሳይፈጸም ሶስት ወር ከዘገየ ከ100% መቀጫ ጋር እንዲፈጸም ሆኖ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

4/ የሪፖርት ማቅረቢያ ቀነ ገደቡ በዕረፍት ወይም በበዓል ቀን ከዋለ ቀጣይ የስራ ቀን የሪፖርት ማቅረቢያ ቀን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18. ስለ ቅጣት

1/ ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ስራ ካካሄደ የደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት አድርጎ እንደጥፋቱ አይነት የሚወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ በአንቀጽ 15 በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሳያሳድስ ቀርቶ በቀጣይ አንድ ወር ውስጥ ከመጣ የአስር ሺ ብር መቀጮ ከፍሎ ፈቃድ ይታደስለታል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 19.የተሻሩ መመርያዎች

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መመርያ ቁጥር 85/2005 በዚህ መመርያ ተሽሯል፡፡

## አንቀጽ 20.መመሪያው ሥራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ተሰጥቶአቸው በሥራ ላይ የሚገኙ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ላይ መመሪያው ከፀደቀ በኋላ ከመጀመሪው የፈቃድ ዕድሳት ወቅት ጀምሮ

የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ፣ የባንክ ዋስትና፣ የዕድሜ ጣሪያ እና ሌሎች ተያያዥ አንቀጾች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ላቀ አያሌው

የገቢዎች ሚኒስትር

## አባሪ

## የብ/ሎ/አ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ

ቀን:...............................

የአመልካቹ ሥምና አድራሻ ስም:........................................ አድራሻ:- ከተማ ...............
ክ/ከተማ.............. ወረዳ .................. የቤት ቁጥር ................ ስልክ ቁጥር .....................

የተጠየቀው የስፖርት ውርርድ ቤት አድራሻ :- ክ/ከተማ................. ወረዳ........... የአካባቢው ልዩ ስም /የህንፃው ስም ...................... የቤት ቁጥር :- ................ስልክ ቁጥር ......................

ስሜ ከላይ የተጠቀሰው አመልካች ...................................... የማመለክተው ጉዳይ በአስተዳደሩ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር .........../20..... አንቀጽ 3 መሠረት ቀጥሎ የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቼ የቀረብኩ /በቀጣይ አስተዳደሩ በሚጠይቀው መሠረት አሟልቼ የማቀርብ /መሆኑ ታውቆ የስፖርት ውርርድ ፈቃድ እንድሰጠኝ እጠይቃለሁ።

### *ተያይዘው የቀረቡ መስረጃዎች:-*

1. የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ሥራ ምክረ ሀሳብ ............... ገጽ
2. የቤት ኪራይ ውል /የባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ
   ተያይዞ ቀርቧል ☐ ለወደፊቱ የሚቀርብ ☐
3. በባንክ ስቴትመንት የተረጋገጠ መነሻ የሥራ ካፒታል /የጥሬ ገንዘብ ማስረጃ
   ተያይዞ ቀርቧል ☐ ለወደፊቱ የሚቀርብ ☐
4. የማህበሩ ዓይነት:-
   የግል ድርጅ/Sole ☐ ኃላ/የተ/የግ/ማህ/PLC ☐ ሌላ ☐
5. ከድርጅቱ ጋር የተዋዋለ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ስም.......................................
   ተያይዞ ቀርቧል ☐ ለወደፊቱ የሚቀርብ ☐
6. የባንክ ዋስትና ብር 1,500,000.00 የሰጠው ባንክ ስም:-..............................................
   ተያይዞ ቀርቧል ☐ ለወደፊቱ የሚቀርብ ☐

7. ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ካሉ

..................................................................................................................................

......................................................................................................................

የአመልካቹ ስም:.................................. ፊርማ:..........................

የዳሬክቶሬቱ አስተያየት ..................................................................................................

..................................................................................................................................

.....................................................................................................................::